የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፰ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 38
ADDIS ABABA, 16th April, 2025

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፪/፪ሺ፲፯
የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ.....
.....ገጽ ፲፰፺፲፪፻፴፩

Content

Proclamation No. 1372/2025
Ethiopian Institute of Certified Public Accountants Establishment Proclamation……
.....Page 18231

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፪/፪ሺ፲፯

የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በመንግሥት እና በግሉ ዘርፍ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት እና የኦዲት ደረጃዎች እንዲተገበሩ መንግሥት የወሰነ በመሆኑ ይህንን ለማስፈጸም በቂ እና ብቁ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ማፍራት በማስፈለጉ፤

የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ለማፍራት እና ሙያውን ለማሳደግ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የሒሣብ ሙያን እና የሒሣብ ባለሙያን በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል ተቋም በማስፈለጉ፤

የሕዝብ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሒሣብ ሙያን እና የሙያተኛውን አቅም ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No. 1372/2025

A PROCLAMATION TO ESTABLISH INSTITUTE OF ETHIOPIAN CERTIFIED PUBLIC ACCOUNTANTS

WHEREAS, the government has decided to implement international financial reporting and auditing standards in governmental and private sectors, it has become necessary to have sufficient and qualified Certified Public Accountants;

WHEREAS, to have Certified Public Accountants and to promote the profession; it is necessary to establish an institution;

WHEREAS, it is necessary to have an Institute that represents the accountancy profession and the professionals both locally and internationally;

WHEREAS, it is important to promote the accountancy profession and the professionals in order to protect the public interest;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

Habtamu Hailemeskel

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፫፻፸፪/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ተማሪ"** ማለት በኢንስቲትዩቱ የተመዘገበ እና በመማር ላይ ያለ ግለሰብ ነው፤

፪/ **"ዕጩ አባል"** ማለት በኢንስቲትዩቱ ለተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ የሚሰጠውን ትምህርት እና ፈተና ያጠናቀቀ ግለሰብ ነው፤

፫/ **"የሒሣብ ሙያ ቴክኒሽያን"** ማለት የሒሣብ ሙያ ቴክኒሽያን ለመሆን በኢንስቲትዩቱ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት እንደ ሒሣብ ሙያ ቴክኒሽያን የተመዘገበ እና የምዝገባ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው ግለሰብ ነው፤

፬/ **"የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ"** ማለት የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ለመሆን በኢንስቲትዩቱ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት እንደተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ የተመዘገበ እና የምዝገባ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው ግለሰብ ነው፤

፭/ **"አባል"** ማለት በኢንስቲትዩቱ እንደተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ የተመዘገበ ግለሰብ ነው፤

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Ethiopian Institute of Certified Public Accountants Establishment Proclamation No 1372/2025".

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ **"Student"** means a person who is registered by the Institute and attending courses of the Institute;

2/ **"Affiliate"** means a person who has completed the courses and examinations of Certified Public Accountants administered by the Institute;

3/ **"Accounting Technician**" means an individual who has met the requirements set by the institute to qualify as an accounting technician and has been registered as an Accounting Technician and hold a certificate of registration;

4/ **"Certified Public Accountant"** means an individual who has met the requirements set by the institute to qualify as a certified public accountant and has been registered as a Certified Public Accountant and hold a certificate of registration;

5/ **"Member"** means an individual who is registered by the Institute as a Certified Public Accountant;

፮/ **"ፌሎው አባል"** ማለት አንድ ግለሰብ የኢንስቲትዩቱ አባል ከሆነ በኋላ በኢንስቲትዩቱ የሚጠየቁ መስፈርቶችን በማሟላቱ የሚገኝ ከፍ ያለ የአባልነት ደረጃ ነው፤

፯/ **"የክብር አባል"** ማለት የክብር አባል ለመሆን በኢንስቲትዩቱ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት እንደ የክብር አባል የተመዘገበ እና የምዝገባ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው ግለሰብ ነው፤

፰/ **"ሲፒኤ (ኢት)"** ማለት የኢትዮጵያ የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ነው፤

፱/ **"ኤቲ(ኢት)"** ማለት የኢትዮጵያ የሒሣብ ሙያ ቴክኒሽያን ነው፤

፲/ **"ኤፍሲፒኤ(ኢት)"** ማለት የኢትዮጵያ ፌሎው የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ነው፤

፲፩/ **"ከፍተኛ የትምህርት ተቋም"** ማለት በከፍተኛ የትምህርት አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

፲፪/ **"መደበኛ ምርመራ"** ማለት ከሙያ ሥነ-ምግባር እና ከተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ጋር በተያያዘ በአባላት ላይ በኢንስቲትዩቱ በቋሚነት የሚደረግ ምርመራ ነው፤

፲፫/ **"ልዩ ምርመራ"** ማለት የሙያ ሥነ-ምግባር ጥሰት መፈፀሙ ጥቆማ ሲቀርብ በማንኛውም ጊዜ ከሙያ ሥነ-ምግባር እና ከተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ጋር በተያያዘ በተማሪዎች እና በአባላት ላይ በኢንስቲትዩቱ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

፲፬/ **"ውስጠ ደንብ"** ማለት በኢንስቲትዩቱ የሚወጣ ኢንስቲትዩቱ የሚመራበት ደንብ ነው፤

፲፭/ **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ ሒሣብ አያያዝና አዲት ቦርድ ነው፤

6/ **"Fellow Member"** means a higher membership status that an individual acquired by fulfilling the requirements set by the Institute after being a member of the Institute;

7/ **"Honorary Member"** means an individual who has met the requirements set by the Institute to qualify as a Honorary Member and has been registered as a honorary member and hold a certificate of registration;

8/ **"CPA (ET)"** means Certified Public Accountant of Ethiopia;

9/ **"AT (ET)"** means Accounting Technician of Ethiopia;

10/ **"FCPA (ET)"** means Fellow Certified Public Accountant of Ethiopia;

11/ **"Institute of Higher Education"** means it shall take the definition given under Higher Education Proclamation;

12/ **"Regular Investigation"** means a recurring investigation undertaken by the Institute on members in relation to professional ethics and continuous professional development;

13/ **"Special Investigation"** means an investigation carried out by the Institute on students and members upon receiving information from the public in relation to violation of ethics and continuous professional development;

14/ **"By-laws"** means the Rules and Regulations issued by the Institute which governs the Institute itself;

15/ **"Board"** means the Accounting and Auditing Board of Ethiopian ;

፲፮/ **"ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

፲፯/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤ እና

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

ክፍል ሁለት

ኢንስቲትዩት ስለማቋቋም

፫. <u>የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት</u>

የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" ተብሎ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በውጪ ሀገር ወይም ሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ቅርንጫፍ ቢሮ ሊከፍት ይችላል፡፡

፭. <u>ዓላማዎች</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የሒሣብ ሙያን ማሳደግ እና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ፤

፪/ የሒሣብ ሙያ የሕዝብ ጥቅምን ማስጠበቁን ማረጋገጥ፤

፫/ የሒሣብ ባለሙያዎች የላቀ እውቀት፣ ክህሎት፣ ሥነ-ምግባር እና የአሠራር ደረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ የሒሣብ ሙያ በሕዝብ ዘንድ ተዓማኒነት እና ዕውቅና እንዲያገኝ ማድረግ፤

16/ **"Ministry"** and **"Minister"** means the Ministry and Minister of Finance respectively;

17/ **"Person"** means any natural or legal person; and

18/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

PART TWO

ESTABLISHING AN INSTITUTE

3. <u>Ethiopian Institute of Certified Public Accountants</u>

Ethiopian Institute of Certified Public Accountants (hereinafter the "Institute") is hereby established by this Proclamation as an Institute having its own legal personality.

4. <u>Head Office</u>

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices abroad or in regions and city administrations in the country as deemed necessary.

5. <u>Objectives</u>

The Institute shall have the following objectives:

1/ Promote the accountancy profession and ensure its sustainability;

2/ Ensure that the accountancy profession protects the public interest;

3/ Enable the accountancy profession to achieve, public trust and recognition, by ensuring that professional accountants adhere to enhanced professional knowledge, skill, ethics and working standards;

፬/ በሀገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የሚኖራቸው ብቁ እና በቂ የሒሣብ ባለሙያዎችን ማፍራት፤ እና

፭/ የሒሣብ ባለሙያዎችን የሙያ ነፃነት ማስከበር ነው።

፮. <u>የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት</u>

፩/ ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላላ ጉባዔ፤

ለ) የአስተዳደር ምክር ቤት፤

ሐ) የሒሣብ ሙያ ትምሕርት፣ ሥርዓተ-ትምሕርት እና የፈተናዎች ኮሚቴ፤

መ) የዲሲፕሊን ኮሚቴ፤

ሠ) የኦዲት ኮሚቴ፤

ረ) ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤ እና

ሰ) አስፈላጊው ሠራተኞች።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል።

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ዓለም አቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ያወጣውን ተማሪዎች እና አባላት የሚመሩበት የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ይቀበላል ወይም ፌደሬሽኑ ከሚያወጣው ደንብ ጋር የተጣጣመ የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ያወጣል፤ ይገመግማል፤ ያሻሽላል፤ ይፋ ያደርጋል፤

4/ Produce sufficient and qualified accountants who are locally and internationally recognized; and

5/ Protect the independence of professional accountants.

6. <u>Organizational Structure of the Institute</u>

1/ The Institute shall have the following organs:

a) general Assembly;

b) governing Council;

c) professional accountancy education, curriculum and examination committee;

d) discipline Committee;

e) audit Committee;

f) chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers; and

g) necessary staffs.

2/ The institute may establish other committees in addition to those specified in Sub-Article (1) of this Article, when it deems necessary to carry out its functions.

7. <u>Powers and Duties of the Institute</u>

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ Adopt or adapt Code of Ethics for Professional Accountants issued by International Federation of Accountants or its successors; or issue, amend and publish a new Code of Ethics which shall be consistent with that of the federation to be followed by its members and students;

Habtamu Hailemeskel

፪/ የተማሪነት ማመልከቻ ይቀበላል፣ ውድቅ ያደርጋል፣ ከተማሪነት ያግዳል፤ ይሰርዛል፤ ለተማሪዎች ፈተና ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ የሚዘጋጅበትን ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ የተማሪዎችን መዝገብ ያደረጃል፤ ጠብቆ ያቆያል፤

2/ Accept or reject students' applications; suspend or cancel students from the register; prepare and administer examinations or facilitate the preparation and administration of the examinations by others; organize and preserve the registers of students;

፫/ የሙያ ትምሕርት፣ የፈተና እና የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና አገልግሎት በእራሱ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰጣል፤

3/ Provide professional education, examinations and continuous professional development training services, on its own or in collaboration with other institutions;

፬/ ተማሪዎች አባል ለመሆን የሚያስችላቸውን እውቀት፣ ክህሎትና እሴት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤

4/ Ensure that students have acquired knowledge, skills and values towards achieving membership objective;

፭/ የአባልነት ማመልከቻ ይቀበላል፣ ውድቅ ያደርጋል፣ ከአባልነት ያግዳል፣ ከአባልነት ይሰርዛል፤ የአባላትን መዝገብ ያደረጃል፤ ጠብቆ ያቆያል፤

5/ Accept or reject membership applications; suspend or cancel members from the register; organize and preserve the registers of members;

፮/ የተማሪዎችን እና የአባላትን መብት፣ ግዴታ፣ ጥቅም እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ይወስናል፤

6/ Determine rights, obligations, privileges and other related matters in relation to students and members;

፯/ የአባላቱን መብት ያስጠብቃል፤

7/ Protect the rights of its members;

፰/ የሒሣብና የኦዲት ሙያን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ መረጃዎችን በመከታተል ለአባላቱ እና ለሕዝብ ያሰራጫል፤

8/ Monitor and disseminate local or international information to members and the public in relation to the accountancy profession;

፱/ ዓለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ያወጣቸውን ደረጃዎች መሰረት በማድረግ የመንግሥት እና የግል ዘርፍ ፍላጎቶችን ማሟላት በሚያስችል አኳኋን የሙያ ብቃት መስፈርቶች፣ የትምህርት ፕሮግራም ይዘቶችን እና ሥርዓተ-ትምህርት ያዘጋጃል፤

9/ Develop qualification requirements, contents of education program and curriculum that meet the needs of both the government and private sectors efficiently and effectively, based on the standards issued by the International Federation of Accountants or its successors;

Habtamu Hailemeskel

፲/ የሙያ ብቃት መስፈርቶች ከፍተኛ ጥራት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና ከልምድ ልውውጥ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል ኢንስቲትዩቱ በፊተና አቅድ ረገድ የዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ወይም እሱን የሚተካ አካል ዕውቅና ካላቸው የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ጋር ጥምረት በመፍጠር በትብብር ይሰራል፤

10/ Establish twinning arrangements with accountancy bodies accredited by the International Federation of Accountants or its successors and work in partnership with them in joint examination schemes for experience sharing and ensuring that the Institute's qualification requirements are of high quality and can command international recognition;

፲፩/ ለአባላት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና መስፈርቶች ያወጣል፣ ሥልጠና ይሰጣል ወይም ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

11/ Set criteria for continuous professional development; provide training or facilitate its provision for members;

፲፪/ በእራሱ አነሳሽነት ወይም ከሌላ ሰው በሚቀርብ ቅሬታ መሠረት በአባላት ወይም በተማሪዎች የሚፈጸም የሥነ-ምግባር ደንብ፣ ይህንን አዋጅ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ውስጠ ደንብ መተላለፍን አስመልክቶ መደበኛ እና ልዩ ምርመራ ያደርጋል፤ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤

12/ Conduct regular and special investigations on any breach of the code of professional conduct and ethics, provision of this Proclamation or by-laws, any students and members, either on its own initiatives or at the request of any person and take disciplinary action where appropriate;

፲፫/ የሒሣብ ሥራ እና የኦዲት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ባለሙያዎችን በተመለከተ ከቦርዱ ጋር የሚኖረውን የዲሲፕሊን ኃላፊነቶች ማቀናጀት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤

13/ Establish procedures for coordination of disciplinary responsibilities with the Board, regarding professionals providing accounting and auditing services;

፲፬/ በተማሪዎች እና በአባላት ላይ የሚጣልን ቅጣት ይወስናል፤

14/ Determine penalties imposed on students and members;

፲፭/ ለሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች በሚያወጣዉ ተመን መሠረት ገቢ ይሰበስባል፤

15/ Collect fees for services rendered at the rate it determined;

፲፮/ አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ደረጃ አውጪ አካላት የሒሣብ፣ የኦዲት፣ የሙያ ትምህርት እና የሥነ-ምግባር ደረጃዎች በሚወጡበት ጊዜ ሙያዊ አስተያየት ይሰጣል፣ ተሳትፎ ያደርጋል፤

16/ Participate and provide opinion when exposure drafts on financial reporting, auditing, educational and ethical standards are prepared by respective international standard setting bodies;

፲፯/ የማማከር፣ የጥናት እና ምርምር አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፰/ የአካውንቲንግ ሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት በተመለከተ የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማትን ያማክራል፤

፲፱/ የኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች በሀገር ውስጥ እና በውጪ አገር እውቅና እንዲያገኙ ይሰራል፤

፳/ ዓላማው እና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ ማናቸውም የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ አካል ጋር ይመካከራል፤ ይተባበራል፤ ግንኙነት ያደርጋል፤ የዚህ አይነቱ አካል አባል ወይም ተባባሪ አባል ይሆናል፤

፳፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤ እና

፳፪/ ዓላማዎቹን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

ክፍል ሦስት
የኢንስቲትዩቱ አካላት እና በኢንስቲትዩቱ ስለሚመዘገቡ ግለሰቦች ምድብ

ምዕራፍ አንድ
የኢንስቲትዩቱ አካላት

፰. ጠቅላላ ጉባዔ

ጠቅላላ ጉባዔው በኢንስቲትዩቱ የተመዘገቡ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎችን እና ኢንስቲትዩቱ በውስጠ ደንብ በሚወስነው መሰረት ድምጽ የሚሰጡ እና የማይሰጡ ግለሰቦችን ይይዛል።

፱. የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን እና ተግባር

ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት ያጸድቃል፤

17/ Provide study, research and consulting services;

18/ Consult Higher Educational Institutions on the preparation of accounting curriculum;

19/ Promote recognition of Ethiopian Certified Public Accountants both locally and internationally;

20/ Consult, cooperate and communicate with, become a member or an affiliate of, any local and international body, the objectives and function of which are similar to those of the institute;

21/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name; and

22/ Perform other related functions necessary for the achievements of its objectives.

PART THREE
ORGANS OF THE INSTITUTE AND CATEGORY OF INDIVIDUALS REGISTERED IN THE INSTITUTE

CHAPTER ONE
ORGANS OF THE INSTITUTE

8. General Assembly

The General Assembly constitutes Certified Public Accountants registered by the Institute and other voting and non-voting individuals determined by by-laws.

9. Powers and Duties of the General Assembly

The General Assembly shall have the following powers and duties:

1/ Approve strategic plan; annual activity plan and annual budget of the Institute;

፪/ የኢንስቲትዩቱን ውስጠ ደንብ፣ መመሪያ እና በተማሪዎች እና በአባላት ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ያወጣል፤ ያሻሽላል፤

2/ Issue by-laws, Directives and code of ethics of the institute enforceable on students and members; amend same;

፫/ የውጭ ኦዲተር ይሰይማል፤ ያሰናብታል፤ የአገልግሎት ጊዜውን ይወስናል፣ ያራዝማል፤

3/ Appoint and dismiss the external auditor, as well as to determine the term and extensions of their service;

፬/ የውጭ ኦዲተር፣ የአስተዳደር ምክር ቤት እና የኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ክፍያ ወይም አበል ይወስናል፤

4/ Determine the amount of fee or allowance to be paid for the services provided by the external auditor, members of the governing council and committees;

፭/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸም፣ የሒሣብ እና የኦዲት ሪፖርት ያጸድቃል፤

5/ Approve performance report, financial statement and audit report of the Institute;

፮/ ከጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ የአስተዳደር ምክር ቤት እና የኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፤ ያሰናብታል፤

6/ Appoint or dismiss candidates for the Governing Council and Committees, who are nominated from the General Assembly;

፯/ የፈተና፣ የዓመታዊ መዋጮ እና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን እና መቀጮዎችን ይወስናል፤

7/ Determine fees for examination, annual subscription, other services; and penalties;

፰/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፯) ሥር የተዘረዘሩትን ሥልጣን እና ተግባራት በከፊል ወይም በሙሉ ለአስተዳደር ምክር ቤት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ እና

8/ May delegate, when it is necessary, its powers and authorities stated under Sub Articles (2) and (7) of this Article, partially or fully to the Governing Council; and

፱/ ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች አካላት በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን እና ተግባር የጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል። ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን ሥልጣን በከፊል ወይም በሙሉ ለአስተዳደር ምክር ቤት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9/ Powers and duties not expressly given to other bodies of the Institute shall be the responsibility of the General Assembly. The General Assembly may, when deemed necessary, delegate this authority, partially or fully, to the governing council.

፲. የአስተዳደር ምክር ቤት

፩/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ስድስት የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች፤ እና

ለ) በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተውጣጡ አምስት አባላት፡፡

፪/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ የአባላት ምርጫ የጾታ ስብጥርን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፬/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡

10. Governing Council

1/ The Governing Council is composed of the following Eleven members:

a) Six Certified Public Accountants elected by the General Assembly; and

b) Five members to be appointed by the government from appropriate government organs and Higher Educational institute.

2/ The Chairperson and Vice Chairperson of the Governing Council shall be Certified Public Accountant.

3/ The appointment of members of the Governing Council shall respect gender composition.

4/ The Governing Council is accountable to the General Assembly.

፲፩. የአስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣን እና ተግባር

የአስተዳደር ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የበጀት አጠቃቀምን እና አፈጻጸምን ይገመግማል፤ ይቆጣጠራል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አባል ለመሆን የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ያጸድቃል፤ ውድቅ ያደርጋል፤ ከአባልነት ያግዳል፤ አባልነትን ከመዝገብ ይሰርዛል፤ የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤

፫/ የአሰራር ሥርዓት እና ሌሎች ሰነዶችን ያወጣል፤ ያሻሽላል፤

፬/ በኮሚቴዎች የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦችን ይመረምራል፤ ያጸድቃል፤ ያሻሽላል፤ ውድቅ ያደርጋል፤

11. Powers and Duties of the Governing Council

The Governing Council shall have the following powers and duties:

1/ Evaluates and monitors budget utilization and performance;

2/ Approve or reject membership application, suspends members or cancel members from register; issue and cancel practicing certificate;

3/ Issue manuals, procedures and other documents; amend same;

4/ Examine, approve, revise and reject resolutions of committee;

፭/ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ ከኢንስቲትዩቱ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ከሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ይተባበራል፤

፮/ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

፯/ ሥልጣንና ተግባሩን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤ እና

፰/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባራት ለዋና ሥራ አስፈጻሚ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

5/ To carry out the responsibilities assigned under this Proclamation, it may cooperate with other similar organizations having similar objectives, either from within or outside the country as necessary;

6/ Execute and cause the execution of the decisions of the General Assembly; perform any other duties assigned by the General Assembly;

7/ Carry out any other necessary activity for the fulfillment of its power and duties; and

8/ May delegate the Chief Executive Officer to perform power and duties listed under this Article.

፲፪. <u>የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን</u>

12. <u>Tenure of office of members of the Governing Council</u>

፩/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የአስተዳደር ምክር ቤት አባል በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

፫/ ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመናት ያገለገለ የአስተዳደር ምክር ቤት አባል ከአንድ የሥራ ዘመን ቆይታ በኋላ በድጋሚ ለአስተዳደር ምክር ቤት አባልነት ሊመረጥ ይችላል፡፡

1/ The term of members of Governing Council shall be Three years.

2/ Notwithstanding the provision of Sub Article (1) of this Article, any member of the Governing Council may be reappointed.

3/ A member of the Governing Council who has served for Two consecutive terms may be reappointed after One term of cooling period.

፲፫. <u>በአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ላይ የተጣለ ገደብ</u>

13. <u>Restrictions Imposed on Members of the Governing Council</u>

የአስተዳደር ምክር ቤቱ አባል ወይም አባሉ ባለአክሲዮን የሆነበት ድርጅት ክፍያ በሚያስገኝ የኢንስቲትዩቱ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

A member of the Governing Council or companies in which he holds shares are not allowed to perform any remunerated duty in the Institute.

፲፬. <u>የሒሣብ ሙያ ትምህርት፣ ሥርዓተ-ትምሕርት እና የፈተናዎች ኮሚቴ አወቃቀር</u>

፩/ የሒሣብ ሙያ ትምህርት፣ ሥርዓተ-ትምሕርት እና የፈተናዎች ኮሚቴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) በአስተዳደር ምክር ቤቱ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ሰብሳቢውን ጨምሮ አራት የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች፣ እና

ለ) በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት እና ከከፍተኛ የትምሕርት ተቋማት የተውጣጡ ሦስት አባላት።

፪/ የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነው። አባላቱ በድጋሚ ለአንድ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ።

፫/ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው።

፲፭. <u>የሒሣብ ሙያ ትምሕርት፣ ሥርዓተ-ትምሕርት እና የፈተናዎች ኮሚቴ ሥልጣን እና ተግባራት</u>

የሒሣብ ሙያ ትምሕርት፣ ሥርዓተ-ትምሕርት እና የፈተናዎች ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ዓለም አቀፍ የትምሕርት ደረጃዎች አውጪ አካል በሚያወጣቸው ደረጃዎች መሠረት ለሒሣብ ሙያ ትምሕርት ብቁ የሚያደርግ ረቂቅ ሥርዓተ-ትምሕርት ይቀርጻል፣ በአስተዳደር ምክር ቤቱ ያጸድቃል፣

14. <u>Composition of Professional Accountancy Education, Curriculum and Examination Committee</u>

1/ The Professional Accountancy Education, Curriculum and Examination Committee is composed of the following Seven members:

a) up on request by the Governing Council, four Certified Public Accountants including the chairperson elected by the General Assembly; and

b) three members to be appointed by the government from appropriate government organs and Higher Educational institutes.

2/ The term of members of the Committee shall be Five years. Members can be re-elected once.

3/ The Committee shall be accountable to the Governing Council.

15. <u>Powers and Duties of Professional Accountancy Education, Curriculum and Examination Committee</u>

The Professional Accountancy Education, Curriculum and Examination Committee shall have powers and duties to:

1/ Formulate a draft syllabus for the award of a professional qualification in accountancy in accordance to international education standard as issued by international federation of accountants (IFAC), cause its approval by the governing council;

Habtamu Hailemeskel

፪/ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ይፈትናል፣ ያርማል፣ ውጤት ይሰጣል ወይም በሌሎች አካላት ፈተና የሚዘጋጅበትን እና የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፫/ የሙያ ሥርዓተ-ትምሕርት አዘገጃጀት፣ የመማሪያ መጻሕፍት አዘገጃጀት፣ የፈተና ዝግጅት፣ አሰጣጥ፣ እርማት፣ የውጤት አሰጣጥ፣ ጥራት እና ሌሎች ፈተናን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከት ረቂቅ የውስጠ-ደንብ እንዲሁም የአሰራር ሥርዓት አዘጋጅቶ ያጸድቃል፣ በጸደቀው መሠረት ይፈጽማል ወይም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፬/ የመማሪያ መጻሕፍት ከሚያዘጋጁ እና ትምሕርት ከሚሰጡ ተቋማት ጋር በትብብር የሚሠራበትን አግባብ የሚወስን ረቂቅ የውስጠ-ደንብ አዘጋጅቶ ያጸድቃል፣ በጸደቀው መሠረት ይፈጽማል ወይም አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፭/ ለአባላቱ የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና መስፈርቶች አዘጋጅቶ ያጸድቃል፣ በእራሱ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ሥልጠና ይሰጣል፣

፮/ የፈተና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ሕጎቹ ተጥሰው ሲገኙ ቅጣት ያስተላልፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፯/ የሒሣብ ሙያ የብቃት ዓይነቶች ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፣

፰/ ሥልጣን እና ተግባሩን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

፱/ ሥልጣን እና ተግባሩን በሚያስፈጽምበት ወቅት ከማንኛውም ሰው ሙያዊ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ እና

2/ Prepare, administer, mark and give result for examinations or facilitate the preparation and administration of the examination by others;

3/ Prepare draft procedure, guidelines and by-laws that determine the preparation of syllabus, text books and examinations; and issues related to administration, marking, giving result, quality and other matters of examinations; and cause its approval; and executes or monitors its performance as approved;

4/ Prepare a draft by-law that determine the manner of collaboration with institutions which prepare textbooks and provide tutorials for students; cause its approval; and executes or monitors its performance as approved;

5/ Prepare requirements for continuous professional development training for its members; and cause its approval; and provide training on its own or in collaboration with other institutions;

6/ Set up examination rules; impose penalties when there is a violation of rules; follow its execution;

7/ Suggest the form of professional qualifications in accountancy to the governing council;

8/ Carry out any other necessary activity for the fulfilment of its power and duties;

9/ Seek technical advice from experts for the fulfilment of its responsibilities; and

Habtamu Hailemeskel

፲/ ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው ውስጠ ደንብ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፮. <u>የዲሲፕሊን ኮሚቴ አወቃቀር</u>

፩/ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) በአስተዳደር ምክር ቤቱ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ሰብሳቢውን ጨምሮ ሦስት የተመሰከረላቸው የሒሣብ ባለሙያዎች፤ ሰብሳቢው በግሉ የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ መሆን የለበትም፤

ለ) ከኢትዮጵያ የፌደራል ጠበቆች ማኅበር የሚመደብ አንድ ጠበቃ፤ እና

ሐ) በመንግሥት የሚሰየሙ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት የተውጣጡ ሦስት አባላት፡፡

፪/ የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፡፡ አባላቱ ለአንድ ጊዜ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

፫/ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው፡፡

፲፯. <u>የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሥልጣን እና ተግባር</u>

የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በተማሪዎች ወይም በአባላት ላይ የሚቀርብ የሕግ እና የሙያ ሥነ-ምግባር ጥሰት ክስ ይመረምራል፣ ይተነትናል፣ ይገመግማል፤ የውሳኔ-ሀሳብ ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ያቀርባል፤ እና

፪/ ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

10/ Perform other functions as provided for in the By-laws issued by the Institute.

16. <u>Composition of Discipline Committee</u>

1/ The Discipline Committee is composed of the following Seven members:

a) Up-on request by the Governing Council, three Certified Public Accountants including the Chairperson elected by the General Assembly; the Chairperson shall not engage in public practice of accounting or auditing;

b) A lawyer appointed by Federal Advocates' Association; and

c) Three members to be appointed by the government from appropriate government organs.

2/ The term of members of the committee shall be Three years. Members can be re-elected once.

3/ The committee is accountable to the Governing Council.

17. <u>Powers and Duties of a Discipline Committee</u>

The committee shall have the following powers and duties:

1/ Examine, analyze, and evaluate cases involving violations of the code of ethics by students or members, and submit recommendations to the Governing Council; and

2/ Perform other functions as provided for in the By-laws issued by the Institute.

Habtamu Haile

Habtamu Hailemeskel

፲፰. የዲሲፕሊን ጥፋት ቅጣት

፩/ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አንድን ክስ ከመረመረ በኋላ ይህ አዋጅ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ውስጠ-ደንብ ወይም የሥነ-ምግባር ደንብ መጣሱን ካረጋገጠ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ እንዲወሰን ለአስተዳደር ምክር ቤቱ የውሳኔ-ሃሳብ ያቀርባል፡-

ሀ) ተግሳጽ ወይም ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፤

ለ) ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ፤

ሐ) ከአባልነት ወይም ከተማሪነት እንዲሰረዝ፤

መ) የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት እንዲመልስ፤

ሠ) በውስጠ ደንብ በሚወሰነው መሰረት የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ፡፡

፪/ ተከሳሹ በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ለሚመለከተው ወንጀልን ለመመርመር ሥልጣን ላለው አካል ይተላለፋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ላይ የተጠቀሱት ውሳኔዎች የተላለፈበት አባል ስሙ እና የተወሰደበት እርምጃ ተገልጾ በኢንስቲትዩቱ ድረ-ገፅ እና ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡

18. Measures against disciplinary violations

1/ After examining a case, if the disciplinary committee determines that the code of ethics; this Proclamation; Regulation, Directive and by-laws issued in accordance with this Proclamation has been violated, it shall submit recommendation, to the Governing Council, to be taken One or more of the following penalties, having regard to the nature and seriousness of the violation:

a) To be reprimanded or cautioned;

b) To be suspended for a period not exceeding Two years;

c) To be canceled from membership or student;

d) The practicing certificate be withdrawn;

e) That the defendant be fined as determined by the by-laws.

2/ The Committee shall transfer the case to the appropriate authority which has the power to investigate criminal activities when the defendant is found in activities which bring criminal liability.

3/ The decisions taken by the Governing Council referred under Sub of Sub Article (b), (c) and (d) of Sub Article (1) of this Article shall be published on the Institute's website and in a widely circulated newspaper containing the name of the member and measures taken against him.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ጠቅላላ ጉባዔው በሚያወጣው የሥነ-ምግባር ደንብ፣ ውስጠ-ደንብ ወይም መመሪያ ላይ የተቀመጡ ሌሎች ቅጣቶች እንዲወሰዱ የውሳኔ ሀሳብ ሊያቅርብ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሰረት በኢንስቲትዩቱ የተጣለ የገንዘብ ቅጣት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንደተወሰነ ቅጣት ተቆጥሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ይቀርብበታል፡፡

4/ Notwithstanding the provision of Sub Article (1) of this Article, the Discipline Committee may recommend other penalties set out in the Code of Ethics, by-laws or Directives issued by the General Assembly.

5/ An administrative fine imposed by the Institute in accordance with this Article shall be deemed to be a fine imposed by a competent court and shall be subject to execution in a regular court.

፲፱. የዲሲፕሊን ክስ የይርጋ ጊዜ

በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የሚቀርብ ክስ ጥፋቱ በተፈጸመ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

19. Period of Limitation of Disciplinary Action

Charges brought in violation of disciplinary rules shall be barred if not brought in One years from the date of the commission of the misconduct.

፳. ይግባኝ ስለማቅረብ

፩/ ጠቅላላ ጉባዔ የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ የሚሰጥ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ያዋቅራል፡፡

፪/ የአስተዳደር ምክር ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው በፍሬ ነገር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፬/ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው የሰጠው ውሳኔ የሕግ ትርጉም ስህተት አለው የሚል ማንኛውም ወገን ውሳኔ በተሰጠ በሥልሳ ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

20. Right to Appeal

1/ The General Assembly shall constitute an Appeal Committee which receive appeals and make decisions.

2/ Any party aggrieved by the decision of the Governing Council, may submit his petition to the Appeals Hearing Committee with in Thirty days of the pronouncement of the decision.

3/ Any decision rendered by the Appeal Hearing Committee on factual matters shall be final.

4/ An appeal may be lodged, with in Sixty days from the pronouncement of the decision, to the Federal High Court on questions of law by any party aggrieved by the decisions of the Appeals Hearing Committee.

Habtamu

፳፩. <u>የኦዲት ኮሚቴ አወቃቀር</u>

፩/ በኢንስቲትዩቱ መደበኛ ሥራዎች ላይ የማይሳተፍ ገለልተኛ የሆነ የኦዲት ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔው ይዋቀራል፡፡

፪/ የኦዲት ኮሚቴው የኦዲት ልምድ ያላቸው ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት ውስጥ የሚመረጡ አንድ ሰብሳቢ እና ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡

፫/ የኦዲት ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፡፡ አባላቱ ለአንድ ጊዜ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

፬/ የኦዲት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡

፳፪. <u>የኦዲት ኮሚቴ ሥልጣን እና ተግባር</u>

የኦዲት ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን፤ የሥነ-ምግባር ደንቦችን መሰረት አድርጎ ሥራዎችን ማከናወኑን እና የኢንስቲትዩቱ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ሕግን የተከተሉ መሆኑን መቆጣጠር፤ መገምገም፤

፪/ በኢንስቲትዩቱ የሚቀርበው የፋይናንስ ነክ ወይም ሌሎች ሪፖርቶች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን መገምገም፤

፫/ ለኢንስቲትዩቱ የውስጥ ኦዲት ክፍል በቂ የሰው ኃይል እና በጀት መመደቡን እንዲሁም ሥራውን በአግባቡ ለመስራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤

፬/ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ ወይም የውጭ ኦዲተር የሚቀጠርበት እና የሚሰናበትበትን ሁኔታ በተመለከተ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ፤

21. <u>Audit Committee</u>

1/ An independent Audit Committee, which does not involve in the regular activities of the Institute, shall be appointed by the General Assembly.

2/ The Audit Committee shall have a Chairperson and Two other members with auditing experience selected from members of the General Assembly.

3/ The term of members of the Audit Committee shall be Three years. Members can be re-elected once.

4/ The Audit Committee shall be accountable to the General Assembly.

22. <u>Power and duties of the audit committee</u>

The Audit Committee shall have the following powers and duties to:

1/ Evaluate and monitor, that the Institute has established an effective internal control system; activities of the Institute are in accordance with Code of Ethics; whether the policies and procedures of the Institute are in accordance with relevant laws;

2/ Assess that the financial or other reports submitted by the Institute are supported by sufficient evidence;

3/ Ensure that adequate human resource and budget are allocated to the internal audit department of the Institute and that there is conducive environment for its proper functioning;

4/ Advise on the conditions of recruitment and dismissal of head of the Internal Auditor or the External Auditor;

ሯ/ የውስጥ ኦዲት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና ከውጭ ኦዲተር ጋር የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት መገምገም፤ ኢንስቲትዩቱ ከውጭ ኦዲተር ጋር ያለውን አጠቃላይ ግንኙነት መምራት፤

ሷ/ የውስጥ እና የውጭ ኦዲተሮች የሰጧቸውን አስተያየቶች ትግበራ መከታተል፤ እና

ሸ/ የውስጥ ኦዲተሩን የሙያ ነፃነት ማረጋገጥ።

5/ Evaluate annual work plan of the Internal Audit Department and working relationship with the External Auditor; to manage overall relationship of the Institute with the External Auditor;

6/ Follow up the implementation of recommendations given by both Internal Auditor and External Auditors; and

7/ Ensure the professional independence of the Internal Auditor.

፳፫. <u>ለአስተዳደር ምክር ቤት እና ለኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ የማያስችሉ ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በማንኛውም ሕግ መሰረት ከስድስት ወር ባላነሰ የእስራት ቅጣት በሚያስቀጣ ወንጀል ተግባር የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈበት ከሆነ፤

ለ) በወንጀል ሕጉ መሰረት እስካልተሰየመ ድረስ በሙስና፣ በስርቆት፣ በአታላይነት፣ በአስመስሎ በመሥራት፣ በሀሰት በመመስከር ወይም በማናቸውም የእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ሥር የተቀመጡት ቅጣቶች የተወሰደበት አባል ከሆነ፤ እና

መ) በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፤ ለአስተዳደር ምክር ቤት ወይም ለኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ ብቁ አይሆንም።

23. <u>Ineligibility for Governing Council and Committee Members</u>

A person shall be ineligible to hold office in the Governing Council or in any committee, if that person:

a) Has, within the past Five years been convicted of a criminal offence under any law punishable by a term of imprisonment of not less than Six months;

b) has been convicted of an offence involving corruption, theft, fraud, forgery, perjury or other acts of dishonesty, unless otherwise reinstated by criminal law;

c) has punished in accordance with Article 18 of this Proclamation; and

d) has been adjudged by a court to be bankrupt.

Hab

፳፬. ከአባልነት ስለመሰናበት

፩/ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የኮሚቴ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ይሰናበታል፡-

ሀ) የሥራ ዘመኑ ሲጠናቀቅ፤

ለ) በእራሱ ፍቃድ ከአባልነት ለመሰናበት ተጠሪ ለሆነለት አካል የጽሁፍ ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

ሐ) ለአባልነት ብቁ ያደረጉት መስፈርቶች ሲጓደሉ፤

መ) በኢንስቲትዩቱ ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሱ እንደአግባብነቱ በጠቅላላ ጉባኤው ወይም በአስተዳደር ምክር ቤቱ ሲወሰን፤

ሠ) በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠበት፤

ረ) በሕግ ወይም በፍርድ ችሎታ ሲያጣ፤

ሰ) የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሞ ሲገኝ፤

ሸ) ለስድስት ወራት ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ የእስራት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ከተሰጠበት፤

ቀ) ኃላፊነቱን በአግባቡ አለመወጣቱ እንደአግባብነቱ በጠቅላላ ጉባዔ ወይም በአስተዳደር ምክር ቤት ሲወሰን፤

በ) በሦስት ተከታታይ ስብሰባዎች ወይም በዓመት ውስጥ ለሦስት ጊዜ ያለበቂ ምክንያት ካልተገኘ፤ እና

ተ) ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፡፡

፪/ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የኮሚቴ አባል ከአባልነት የሚሰናበትበት ሂደት እና ክፍት ቦታው የሚሞላበት ሁኔታ በውስጠ ደንብ ይወሰናል፡፡

24. Dismissal from Membership

1/ A person shall dismissed from holding office of the Governing Council or Committee, if:

a) term of office expires;

b) submits resignation request, in writing, to the body he is accountable to;

c) no longer fulfills the requirements considered at the time of his appointment;

d) behavior contradicts with the interests of the Institute determined by the General Assembly or Governing Council, as appropriate;

e) has been declared by a court to be bankrupt;

f) has been juridically or legally interdicted;

g) violates Code of ethics;

h) has definitely sentenced to a term of imprisonment equal to or exceeding Six months;

i) has judged by the General Assembly or Governing Council, as may be appropriate, that he is no longer able to perform his duties;

j) is absent in meetings for Three consecutive times or Three times within a year, with no justified reasons; and

k) passes away.

2/ The procedure for ceasing a member from the Governing Council and Committees and filling of the vacant shall be determined by by-laws.

፳፭. <u>ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ስለመቅጠር</u>

፩/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው ውስጠ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት ዋና ሥራ አስፈጻሚን እና ምክትል ሥራ አስፈጻሚዎችን አወዳድሮ ይቀጥራል፡፡

፪/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው፡፡

25. <u>Hiring Chief Executive Officers and Deputy Chief Executive Officer</u>

1/ The Governing Council shall hire Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers in accordance with by-laws or Directive issued by the institute.

2/ The Chief Executive Officer shall be accountable to the Governing Council.

፳፮. <u>የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣን እና ተግባር</u>

ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኢንስቲትዩቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያስተባብራል፤ ያስተዳድራል፤ ይከታተላል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት እና የሥራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

፫/ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ያቀርባል፤

፬/ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የሚመሩበትን የሥራ ደንብ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

፭/ በኢንስቲትዩቱ ውስጠ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ አፈጻጸማቸውን ይገመግማል፤

፮/ የኢንስቲትዩቱን ንብረቶች ያስተዳድራል፤

፯/ ተማሪ፣ ዕጩ አባል፣ አባል፣ ፌሎው አባል ሆኖ ለመመዝገብ ወይም የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ይቀበላል፤

፰/ የአባላት ዝርዝር መረጃዎች በየዓመቱ እንዲታተም ያደርጋል፤

26. <u>Powers and Duties of the Chief Executive Officer</u>

The Chief Executive Officer shall have the following powers and duties:

1/ Coordinate, administer and monitor the day-to-day activities of the institute;

2/ Prepare and submit annual budget and work plan of the institute; implement same upon approval; submit annual performance report;

3/ Submit budget performance report within Three months of the end of the fiscal year;

4/ Prepare work rules for the staff of the institute; and implement same upon approval;

5/ Hire and administer employees of the Institute and evaluate their performance in accordance with the by-laws and Directives of the Institute;

6/ Administer properties of the Institute;

7/ Receive applications to, be a student, affiliates, members, fellow members and get practicing certificate;

8/ Cause annual publication of particulars of the members;

፱/ የሂሣብና የኦዲት ሙያን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ መረጃዎችን በመከታተል ለአባላቱና ለሕዝብ ያሰራጫል፤

፲/ የኢንስትቲዩቱን አባላት እና ተማሪዎች መዝገብ ያደረጃል፤ ጠብቆ ያቆያል፤

፲፩/ በስብሰባ ላይ እንዳይገኝ ካልተወሰነ በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በማናቸውም የጠቅላላ ጉባዔ እና የአስተዳደር ምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፤

፲፪/ በጠቅላላ ጉባኤው እና በአስተዳደር ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤ እና

፲፫/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል።

9/ Disseminate local or international information to members and the public in relation to the accountancy profession;

10/ Administer and preserve the registers of members and students;

11/ Attend, unless otherwise excused, any meetings of the General Assembly and Governing Council without voting rights;

12/ Perform any other duties assigned by the General Assembly and Governing Council; and

13/ Represent the Institute in its dealings with third parties.

፳፯. <u>የምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣን እና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤ እና

፪/ በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናል።

27. <u>Powers and Duties of the Deputy Chief Executive Officer</u>

The Deputy Chief Executive Officer shall have the following powers and duties:

1/ Act on behalf of the Chief Executive Officer in his absence; and

2/ Perform tasks assigned to him the Chief Executive Officer.

፳፰. <u>በኢንስቲትዩቱ ውስጠ-ደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ውስጠ-ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡-

፩/ የጠቅላላ ጉባዔ ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት እና የኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና ስብሰባን የሚመለከቱ ጉዳዮች፤

፪/ የአስተዳደር ምክር ቤት እና የኮሚቴ አባላት የምርጫ ሥነ-ሥርዓት፤

28. <u>Issues to be Determined by the Institutes by-laws</u>

The institute may issue by-laws regarding the following matters:

1/ The procedure for convening General Assembly, Governing council and committee meetings and other related matters;

2/ The procedure for electing the Governing Council and committee members;

፫/ የዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ሠራተኞች የቅጥር ሁኔታ፤

፬/ የተማሪ ቅበላ፣ የሒሳብ ሙያ ቴክኒሻያን፣ የተመሠከረለት የሒሳብ ባለሙያ፣ ፌሎው አባል እና የክብር አባል መስፈርት፤

፭/ በሌላ ሀገር የሒሣብ ሙያ ማኅበር የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ሆኖ የተመዘገበ ግለሰብ በኢንስቲትዩቱ ስለሚመዘገብበት ሁኔታ፤

፮/ ስለኢንስቲትዩቱ የትምህርት አሰጣጥ፣ ትምህርቱ ስለሚወስደው ጊዜ፣ ስለፈተና፣ የማለፊያ ነጥብ እና ተያያዥ ጉዳዮች፤

፯/ የውጭ ኦዲተር አሰያየም፤

፰/ የኢንስቲትዩቱን የባንክ ሒሣብ ከመክፈት እና ከማንቀሳቀስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እና ከኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግባር ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት፡፡

3/ The recruitment of the Chief Executive Officer, Deputy Chief Executive Officer, and personnel;

4/ The requirements for student admission; criteria for Accounting Technicians, Certified Public Accountants, Fellow Members, and Honorary Members;

5/ The registration requirements at the institute for an individual accredited as a Certified Public Accountant by a foreign professional accounting body;

6/ The institute's educational modalities, duration, examinations, passing scores, and related matters;

7/ The appointment of an external auditor;

8/ Matters pertaining to the opening and transaction of the institute's bank account as well as other issues related with powers and duties given to the institute.

ምዕራፍ ሁለት
በኢንስቲትዩቱ ስለሚመዘገቡ ግለሰቦች ምድብ

CHAPTER TWO
CATEGORY OF INDIVIDUALS REGISTERED IN THE INSTITUTE

፳፱. ምድብ

በኢንስቲትዩቱ የሚመዘገቡ ግለሰቦች በሚከተሉት ምድቦች ሊጠሩ ይችላሉ፡-

፩/ ተማሪ፤

፪/ ዕጩ አባል፤

፫/ የሒሣብ ሙያ ቴክኒሺያን፤

፬/ አባል፤

፭/ ፌሎው አባል፤

፮/ የክብር አባል፤ እና

፯/ ኢንስቲትዩቱ በውስጠ ደንብ የሚወስናቸው ሌሎች ምድቦች፡፡

29. Category

Individuals registered by the Institute may be designated in the following categories:

1/ Student;

2/ Affiliate;

3/ Accounting Technician;

4/ Member;

5/ Fellow Member;

6/ Honorary Member; and

7/ Other categories determined by by-laws of the Institute.

፴. <u>የሒሣብ ባለሙያዎች መጠሪያ</u>

፩/ በኢንስቲትዩቱ የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ሆኖ የተመዘገበ ግለሰብ እራሱን የኢትዮጵያ የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ እና ሲፒኤ (ኢት)፤ ፌሎው አባል ከሆነ ኤፍሲፒኤ (ኢት) ብሎ መጥራት ይችላል፡፡

፪/ በኢንስቲትዩቱ የሒሣብ ሙያ ቴክኒሺያን ሆኖ የተመዘገበ ግለሰብ ኤቲ (ኢት) ብሎ መጥራት ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሰው ባለሙያ ከላይ የተጠቀሰውን ምህጻረ-ቃል ከስሙ በኋላ መጠቀም ይችላል፡፡

፴፩. <u>የተከለከለ ሙያዊ ሥያሜ እና ምህጻረ-ቃል</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ ሥር ከተጠቀሰው ውጪ የሒሣብ ባለሙያዎችን ሥያሜ እና መለያ ምህጻረ-ቃል መጠቀም አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ወይም የሒሣብ ሙያ ቴክኒሺያን ከተመዘገበበት ምድብ ውጪ ያለን ሙያዊ ሥያሜ እና ምህጻረ-ቃለ መጠቀም አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ስር የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ጥሶ የተገኘ ግለሰብ በኢንስቲትዩቱ የባለሙያዎች የሥነ-ምግባር ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

30. <u>Designations of Accountants</u>

1/ A Certified Public Accountant of the Institute shall be entitled to call himself as Certified Public Accountant of Ethiopia and to use the letters CPA (ET); and Fellow member to use the letters FCPA (ET).

2/ An Accounting Technician of the Institute shall be entitled to call himself as Accounting Technician Ethiopia and to use the letters AT (ET).

3/ Persons indicated in Sub Article (1) and (2) of this Article are entitled to use the respective letters after their name.

31. <u>Prohibited Use of Members' Designated Letters</u>

1/ No person shall use the designated letters of accountants except as provided in Article 30 of this Proclamation.

2/ No Certified Public Accountant or Accounting Technician of the Institute shall use designated letters for a category of which he is not registered in.

3/ Any person in contravention with Sub Article (1) and (2) of this Article shall be punished in accordance with the Institute's code of ethics.

ክፍል አራት

የኢንስቲትዩቱ የገቢ ምንጭ እና ንብረት አጠቃቀም

፴፪. የኢንስቲትዩቱ የገቢ ምንጭ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

፩/ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያ፤

፪/ የተማሪዎች ዓመታዊ ክፍያ፤

፫/ ከፈተና የሚገኝ ገቢ፤

፬/ ከሥልጠና፣ ከኮንፈረንስ እና ከሴሚናር የሚገኝ ገቢ፤

፭/ ከተለያዩ የሕትመት ሽያጮች የሚሰበሰብ ገቢ፤

፮/ ከማማከር ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

፯/ ከጥናት፣ ከምርምር እና ከሚሰጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ገቢ፤

፰/ ስጦታ እና ድጋፍ፤ እና

፱/ ሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች።

፴፫. የኢንስቲትዩቱ ገንዘብ እና ንብረት

የኢንስቲትዩቱ ገንዘብ እና ንብረት በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቁ ሥራዎችን ለማከናወን ይውላል።

፴፬. የባንክ ሒሣብ እና የሒሣብ መዝገብ

፩/ የኢንስቲትዩቱ ገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ፈቃድ አግኝተው በሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ባንኮች ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

፪/ ኢንስቲትዩቱ ሕግን የተከተለ እና የተሟላ የሒሳብ ሰነዶችን፣ መዛግብትን ይይዛል፤

፫/ ኢንስቲትዩቱ ቦርዱ በተቀበለው ወይም ባወጣው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች መሰረት የፋይናንስ ሪፖርቱን ማዘጋጀት አለበት።

PART FOUR

SOURCES OF FUNDS AND UTILIZATION OF PROPERTIES OF THE INSTITUTE

32. Sources of Funds of the Institute

The Institute shall have the following source of funds:

1/ Annual membership subscription fees;

2/ Annual student'S subscription fees;

3/ Examination fees;

4/ Revenues from training, conferences and seminars;

5/ Revenue from sales of various prints;

6/ Revenue from consultancy service;

7/ Revenue from study, research and other services provided;

8/ Grants and subsidies; and

9/ Other legal sources.

33. Funds and Property of the Institute

The funds and assets of the Institute shall be used to carry out the activities approved by the General Assembly.

34. Bank and Books of Accounts

1/ The funds of the Institute shall be deposited in any banks operating in Ethiopia with a legal license.

2/ The Institute shall keep accounting records and documents in accordance with relevant laws.

3/ The Institute shall prepare the financial reports in accordance with the financial reporting framework as adopted by the Board.

Habtamu Hailemeskel

፴፭. አዲት ስለማስደረግ

፩/ የኢንስቲትዩቱ የሒሣብ ሪፖርቱ እና የሒሣብ መዛግብት በየዓመቱ በውጪ ኦዲተር መመርመር አለበት፡፡

፪/ በውጪ ኦዲተር የተመረመረው የሒሣብ ሪፖርት የሒሣብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ለጠቅላላ ጉባዔው መቅረብ አለበት፡፡

፫/ የጸደቀውን የኦዲት ሪፖርት በኢንስቲትዩቱ ድረ-ገፅ ላይ እንዲቀመጥ እና ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣቸው የተለያዩ ሕትመቶች እንዲሰራጨ መደረግ አለበት፡፡

፴፮. የውጭ ኦዲተር ሆኖ ስለመሰየም

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ የኦዲት ሥራ ለመስራት ፈቃድ ያለው ሰው ኦዲተር ሆኖ ሊመረጥ ይችላል፡፡

፪/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ አባል የሆነ ማንኛውም የኢንስቲትዩቱ አባል ኦዲተር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም፡፡

፫/ የሚመረጠው ኦዲተር የአገልግሎት ዘመን ከሦስት ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም አንድ የውጪ ኦዲተር ከሦስት ዓመታት ቆይታ በኋላ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

፴፯. የበጀት ዓመት

የኢንስቲትዩቱ የበጀት ዓመት ከሐምሌ ፰ እስከ ሰኔ ፴ ነው፡፡

ክፍል አምስት

ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤት ስለ ማቋቋም

፴፰. መቋቋም

፩/ ኢንስቲትዩቱን የሚመራ ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

35. Audit of Accounts

1/ The Institute's financial statements and financial records shall be audited annually by an external auditor.

2/ The financial report audited by the external auditor shall be submitted to the General Assembly within Four months of the end of the financial year.

3/ The approved audit report shall be made available on the Institute's website and shall be distributed in various publications of the Institute.

36. Appointment as an External Auditor

1/ A person licensed to practice audit in Ethiopia may be appointed as an Auditor.

2/ No member of the Governing Council may be appointed as an Auditor.

3/ The term of office of the appointed Auditor shall not exceed Three years.

4/ Notwithstanding the provision of Sub Article (3) of this Article, the External Auditor may be reappointed after a Three years cooling period.

37. Fiscal Year

The fiscal year of the Institute is from July 8 to July 7 of the following year.

PART FIVE

ESTABLISHMENT OF INTERIM GOVERNING COUNCIL

38. Establishment

1/ An Interim Governing Council, that administers the Institute is hereby established by this Proclamation.

፪/ የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከሰባት ዓመት አይበልጥም፡፡

፫/ ኢንስቲትዩቱ በጊዜያዊ አስተዳደር ወቅት ተጠሪነቱ ለቦርዱ ነው፡፡

፬/ ለጊዜያዊ አስተዳደሩ የፕሮጀክት ኃላፊ እና አስፈላጊው ሠራተኞች ይቀጠራሉ፡፡

፭/ የፕሮጀክቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው፡፡

2/ The term of office of the Interim Governing Council shall not exceed Seven years.

3/ The Institute shall be accountable to the Board, for the Interim period.

4/ A Project Manager and other required staff, for the Interim period, shall be hired.

5/ The Project Manager shall be accountable to the Interim Governing Council.

፴፱. <u>ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤት አወቃቀር</u>

ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየሙ የሚከተሉት ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ ከቦርዱ የሚመደብ ሰብሳቢ፤

፪/ ሁለት የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች (ሲ.ፒ.ኤ.)፤

፫/ ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚመደብ አንድ ሰው፤

፬/ ከከፍተኛ የትምሕርት ተቋም የሚመደብ ሁለት መምህራን ወይም ተመራማሪዎች፤ እና

፭/ ከትምሕርት ሚኒስቴር የሚመደብ አንድ ሰው፡፡

39. <u>Composition of the Interim Governing Council</u>

The Interim Governing Council shall have the following Seven members appointed by the Government on the recommendation by the Minister:

1/ A Chairperson appointed from the Board;

2/ Two Certified Public Accountants;

3/ One person from Ministry of Finance;

4/ Two lecturers or researchers from a Higher Education Institution; and

5/ One person from Ministry of Education.

፵. <u>የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባ</u>

፩/ ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል ቢያንስ አራት የሚሆኑት ሲጠይቁ በማንኛውም ጊዜ ልዩ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

40. <u>Meeting of the Interim Governing Council</u>

1/ The Interim Governing Council shall meet at least once in a month; the Council may hold a meeting at any time upon the request by the Chairperson or upon request of at least Four of its members.

፪/ በማንኛውም የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባ ሰብሳቢውን ወይም ሰብሳቢውን የ ሚወክለው ጨምሮ ከአባላቱ ቢያንስ አራቱ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

2/ There shall be a Quorum where at least Four members including the Chairperson or his representative are present at any meeting of the Interim Governing Council.

፫/ ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

3/ Decisions of the Interim Governing Council shall be passed by a majority vote; however, the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

፬/ የፕሮጀክት ኃላፊው በስብሰባ ላይ እንዳይገኝ ካልተወሰነ በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፡፡

4/ Unless otherwise excused, the Project Manager may attend any meeting of the Interim Governing Council, without voting right.

፵፩. <u>የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣን እና ተግባር</u>

ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

41. <u>Powers and duties of the Interim Governing Council</u>

The Interim Governing Council shall have the following powers and duties:

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ለኢንስቲትዩቱ የተሰጡ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤

1/ Oversee the duties assigned, to the Institute, under Article 7 of this Proclamation;

፪/ ለቦርዱ የሚቀርበውን የኢንስቲትዩቱን በጀት፣ የሥራ ፕሮግራም እና ሪፖርት ይመረምራል፤

2/ Review the budget, work program and reports of the Institute prior to their submission to the Board;

፫/ የኢንስቲትዩቱን የፕሮጀክት ኃላፊ ይቀጥራል፤ ያሰናበታል፤

3/ Hire and terminate contract of the Project Manager;

፬/ የፕሮጀክት ኃላፊውን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤

4/ Evaluate Project Manager performance;

፭/ የፕሮጀክት ኃላፊውን እና የሠራተኞችን የሥራ ሁኔታ ይወስናል፤

5/ Determine terms of employment of the Project Manager and staff;

፮/ የፕሮጀክቱን ኃላፊ እና የሌሎች ሠራተኞችን ክፍያ በሚኒስቴሩ ያጸድቃል፤

6/ Cause the approval of payment for the Project Manager and other staffs, by the Ministry;

፯/ ኢንስቲትዩቱ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠየቀውን የክፍያ ተመን በሚኒስቴሩ ያጸድቃል፤

7/ Cause the approval of tariff for services provided by the Institute, by the Ministry;

፰/ ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ በተቋቋመ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተመሠከረላቸው የሒሣብ ባለሙያ የሆኑ መስራች አባላትን ይመዘግባል ወይም እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤ ለጊዜያዊ አስተዳደሩ የሚያገለግል ውስጠ ደንብ አዘጋጅቶ የተመዘገቡ አባላትን በመጥራት ያጸድቃል፤

8/ Register the founding members of Certified Public Accountant or cause the registration within Six months of its establishment; prepare By-laws applicable for the interim period; convene registered members and cause approval of By-laws;

፱/ የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከመጠናቀቁ ከስድስት ወራት በፊት የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ እና (ሠ) ሥር ለተጠቀሱት አካላት ከጠቅላላ ጉባዔ የሚወከሉ አባላትን ያስመርጣል፤

9/ Convene General Assembly's meeting Six months before the end of the Interim Governing Council term; chair the meeting; and among members of the General Assembly, cause the election of members for the organs stated under Sub of Sub Article (b), (c), (d) and (e) of Sub Article (1) of Article 6 of this Proclamation;

፲/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ እና (ሠ) ሥር ለተጠቀሱት አካላት ከመንግሥት፣ ከከፍተኛ የትምሕርት ተቋማት እና ከኢትዮጵያ የፌደራል ጠበቆች ማኅበር የሚወከሉ አባላት እንዲመደቡ ያደርጋል፤

10/ Cause the appointment of members for the organs stated under Sub of Sub Article (b), (c), (d) and (e) of Sub Article (1) of Article 6 of this Proclamation, who shall be comprised of Government, Higher Education Institutions and Federal Advocates' Association;

፲፩/ ኢንስቲትዩቱ የዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ተባባሪ አባል ሆኖ እንዲመዘገብ፤ እንዲሁም በፋይናንስ፣ በአደረጃጀት እና በባለሙያ አቅም እንዲጠናከር ያደርጋል፤

11/ Cause registration of the Institute as an Associate Member of the International Federation of Accountants; strengthen Financial, Organizational and Professional Capacity of the Institute;

፲፪/ በሥራ ዘመኑ ጊዜ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ያሻሽላል፤

12/ Issue and amend Directives for the effective implementation of this Proclamation during the interim period;

Habtamu Hailemeskel

፲፫/ ዓላማው እና ተግባሩ ተመሳሳይ ከሆነ የሙያ ማኅበር እና ከማናቸውም ዓለም አቀፍ ተቋም ጋር በሚደረግ ግንኙነት ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤ እና

፲፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣን እና ተግባሩን በከፊል ለፕሮጀክት ኃላፊው በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፵፪. <u>የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት አበል</u>

የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት የሚከፈላቸው የአበል መጠን በሚኒስቴሩ ይወሰናል።

፵፫. <u>ኃላፊነትን ስለማስረከብ</u>

፩/ ኢንስቲትዩቱ የዓለም አቀፍ የሒሳብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ተባባሪ አባል ሲሆን፤ እንዲሁም በፋይናንስ እና በአደረጃጀቱ የተጠናከረ መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲወስን ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ኃላፊነቶቹን ለኢንስቲትዩቱ የአስተዳደር ምክር ቤት ያስረክባል።

፪/ ርክክብ ከመፈጸሙ በፊት ኢንስቲትዩቱ በውጪ ኦዲተር መመርመር አለበት።

፫/ ርክክቡ በሰባት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሚኒስቴሩ በሚወክለው አካል ይፈጸማል፤ ርክክቡ ሲጠናቀቅ የጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይጠናቀቃል።

፬/ ርክክብ ከተፈጸመ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ኢንስቲትዩቱ በቦርዱ በመመዝገብ እንደ የሒሣብ ሙያ ማኅበር ዕውቅና ማግኘት እና ለቦርዱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

13/ Represent the Institute in its dealings with professional association and international body, the objectives and functions of which are similar to those of the institute; and

14/ Where necessary may delegate its power to the Project Manager partially.

42. <u>Allowance for members of the Interim Governing council</u>

The amount of allowance paid to members of the Interim Governing Council shall be determined by the Minister.

43. <u>Transfer of Responsibility</u>

1/ The Interim Governing Council shall transfer its responsibilities to the Institute's Governing Council, upon the Institute, being an Associate Member of the International Federation of Accountants; decision is made by the Ministry that the Institute is financially viable, and appropriate governance is in place.

2/ Prior to transfer, the Institute shall be audited by an external auditor.

3/ The transfer shall be effected with in Seven years by a representative assigned by Ministry; upon the transfer, the term of office of the Interim Governing Council shall cease.

4/ Within Six months of the transfer, the Institute shall be registered with the Board and accredited as a Professional Accountancy Body; submit report to the Board.

፵፬. በጀት

፩/ የኢንስቲትዩቱ በጀት ከመንግሥት የሚገኝ ድጋፍን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ የሚሰበሰበውን ገቢ ያጠቃልላል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ መሠረት የሚሰበስበው ገቢ ወጪውን ለመሸፈን በቂ እስከሚሆን ድረስ የበጀት ድጋፉ ይቀጥላል፡፡

፫/ የኢንስቲትዩቱን የበጀት አጠቃቀም ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ይወስናል፡፡

፬/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ ከመንግሥት የሚያገኘውን የበጀት ድጋፍ በተመለከተ የሒሣብ መዛግብቱ እና ገንዘብ ነክ ሰነዶቹ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፭. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ፣ ኢንስቲትዩቱ እና ጊዜያዊ የአስተዳደር ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ተግባር ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

44. Budget

1/ The Institute budget is constituted subsidy from the government and revenue collected according to Article 32 of this Proclamation.

2/ The government subsidy shall continue until the revenue collected in accordance with Article 32 of this Proclamation is sufficient to cover all the expenses of the Institute.

3/ The Interim Governing Council shall determine the budget allocation and utilization of the Institute.

4/ Subject to Article 35 Sub Article (1) of this Proclamation, with respect to the government's budgetary support, the institute's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Federal Auditor General or an auditor assigned by the Federal Auditor General.

PART SIX
MISCELLANEOUS PROVISIONS

45. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Board, the institute and the Interim Governing Council may issue Directives to exercise the powers and duties assigned to each of them in this Proclamation.

፵፮. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፯/፪ሺ፮ እና በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፱/፪ሺ፯ ድንጋጌዎች ተሽረዋል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ልማድ ወይም አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፵፯. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት

46. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ The provisions of the Financial Reporting Proclamation No. 847/2014 and the Establishment and Determination of the Procedure of Accounting and Auditing Board of Ethiopia Council of Ministers Regulation No. 332/2014 are hereby repealed with respect to matters provided for in this Proclamation.

2/ No law, customary or other practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

47. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 16th day of April, 2025

TAYE ATSKE SELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF
ETHIOPIA